# የዜጎች መድረክ

ኢዜማ

ቅፅ 2 ቁጥር 71 ጥር 06 ቀን 2013ዓ.ም
በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ

## የትግራይ ፈተና እና የመቀሌ ቆይታዩ

( ተክሌ በቀለ)



# የኢዜማ ወረዳ 28 የዕጩዎች ምርጫ ምን ይመስል ነበር?

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የፊታችን ግንቦት መጨረሻ በሚካሄደው 6ኛው ሀገር አቀፍ ምርጫን ተከትሎ ለምርጫው በእጩነት የሚያቀርባቸውን እጩዎች ምልመላ ሲያካሄድ ቆይቷል፡፡ እጩዎቻቸውን ከለዩት የኢዜማ ምርጫ ወረዳዎች መሀል የኢዜማ ሊቀመንበር አቶ የሺዋስ አሰፋ የሚገኙበት የኢዜማ አዲስ አበባ ምርጫ ወረዳ 28 አንዱ ነው፡፡ በዚህ ወረዳ የተደረገውን ምርጫ፣ የወረዳው የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ሄኖክ ለይኩን እንደሚከተለው ያስቃኙናል፡፡

## መግቢያ

በሰለጠነ ሕዝብና በሰለጠነ ፖለቲካ ውስጥ አንድን ማኅበረሰብ የሚወክሉ የሕዝብ ተወካዮች በዋናነት ከሚወክሉት ሕዝብ ጋር የቀረበ ግንኙነት ሊኖራቸው፣ የሕዝባቸውንም ችግር አብረው ሊጋሩ፣ መፍትሔም በጋራ ሊፈልጉ ይገባል። በአኗኗር፣ በማኅበረሰባዊ ትስስር፣ በሥነ ልቦና ወዘተ የሕዝብ ተወካዮች ከአካባቢው ነዋሪ ሕብረተሰብ ጋር የተቀራረቡ መሆን አለባቸው።በማይገባ አካሄድ በፖለቲካዊ ውሳኔ አንድን ‹‹የሕዝብ ተወካይ›› ቋንቋን ብቻ መሠረት አድርጎ “ወከል” የሚል የፖለቲካ መንገድ ላለፍት ረዥም ዓመታት ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ዋጋ አስከፍሏል፡፡ ይህ ጎጂ የፖለቲካ ባህል መቅረት አለበት። ሕብረተሰቡም ይሄን አካሄድ ለሚከተሉ ተወካይ ነን ብለው ለሚቀርቡ ወገኖች ድምፅ ባለመስጠት በዚህ መንገድ ተሞክሮ ያላዋጣውን ውክልና በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ እንዲቀርና እንዲስተካከል የራሱን ድርሻ መወጣት አለበት።

ኢዜማ ትክክለኛውን የፌዴራል አደረጃጀት በመከተል አዋጭ የእጩ አቀራረብ አካሔድ ሀገራችን እንድትለምድ አንድ ብሎ ጀምሯል። ሌሎችም የፖለቲካ ፓርቲዎች ይህን ባህል እንዲለምዱ መንገዱን ለማሳየት እየሞከረ ይገኛል፡፡ ለሕብረተሰቡም እንደ ጥሩ መንገድ አሳይቷል። ለዚህም ማሳያ እንዲሆን የኢዜማ የምርጫ ወረዳ 28 ዕጩ አመራረጥ በጥቂቱ እንቃኝ፡፡

ጥር 02 ቀን 2013 ዓ.ም ኢዜማ በምርጫ ወረዳ 28 በቀጣይ ሀገራዊ ምርጫ ወረዳውን የሚወክሉ እጩዎችን በጠቅላላ ጉባኤ ከማስመረጡ በፊት በኢዜማ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ወረዳውን የሚወክሉ የወረዳው ተወላጅ ወይም ነዋሪ በጽ/ቤት አማካይነት በተጠቀሰው መስፈርት መሠረት የተጠየቁትን መረጃ ሁሉ ገቢ አድርገዋል።

በየካቲት 07 ቀን 2012 ዓ.ም በተካሄደው የምርጫ ወረዳው ጠቅላላ ጉባኤ በአባላት ሶስት የምርጫ እጩ መዛኝ/መልማይ ኮሚቴ ተመርጠው ነበር። ከኮሚቴው በተጨማሪ የወረዳው ሊቀመንበርና ፀሐፊ ከነዚሁ ሦስት የተመረጡ የምርጫ እጩ መዛኝ/መልማይ ኮሚቴ ጋር በጋራ አምስት ሆነው በደንቡ መሠረት ለማስፈፀም በጠቅላላ ጉባኤው ፊት በታማኝነት የተሰጣቸውን ኃላፊነት በአግባቡ እንደሚወጡ ቃል ገብተው የነበሩ መሆኑ ይታወቃል። በዚህም መሰረት በተቋቋመው ኮሚቴ (5 አባላት ያሉት) አማካይነት ማንኛውም የወረዳው ተወላጅ ወይም ነዋሪ ለወረዳው በእጩ ተመራጭነት ወረዳውን ወክሎ መወዳደር የሚፈልግ ከሆነ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ መስፈርት እንዲያሟሉ በጽ/ቤት ግድግዳ ላይ ተለጥፏል። መስፈርቶቹ፡-

- የኢዜማ አባልነት ግዴታውን የተወጣ (በወረዳውም አባል የሆነ)
- የስድስት ወራት ወርሀዊ ክፍያ በምርጫ ወረዳው መክፈሉ የተረጋገጠ፣
- ኢዜማ ባስቀመጠው የትምህርት ዝግጅት መሥፈርት፣
- በማንኛውም ወንጀልና በሕግ ተፈላጊ ከመሆን ነፃ የሆነ፣
- በሀገሪቱ ሕግ መሠረት የመምረጥ ሆነ የመመረጥ መብቱን ያልተገደበ፣
- ሥነ-ምግባር፣ ከማንኛውም ሱስ ነፃ የሆነ፣ ተዓማኒ፣
- በማኅበረሰቡ ዘንድ ያደረገው መልካም ተሳትፎዎችን የሚገልጽ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣
- የምርጫ ቅስቀሳ ወጪን በፐርሰንት ራሱ የሚወዳደረው ተወካይ መሸፈን የሚችል ናቸው።

እነዚህ መስፈርቶች ዋና ዋና ጉዳዮች ቢሆኑም በወረዳውም ሆነ በማዕከል የፓርቲ አመራር ውስጥ የሚገኝ ተወዳዳሪ ዕጩ ሆኖ መቅረብ ከፈለገ ከአንድ ወር በፊት በራሱ ፈቃድ፣ በደብዳቤ ኃላፊነቱን መልቀቅ ይጠበቅበታል። ለሴቶችና ለአካል ጉዳተኞች የማበረታቻ ሰፊ እድሎች እንደተጠበቁ ሆኖ፤ ለወረዳው እጩ ሆኖ ለመቅረብና ለመመረጥ ከላይ የተዘረዘሩ መስፈርቶች በማሟላትና በኢዜማ የተዘጋጀ ፎርም በመሙላት በጽ/ቤት በኩል ለእጩ መልማይ ኮሚቴ ገቢ ያደርጋል።

## በወረዳችን የተከወኑ ድርጊቶች

በአምስት አባላት የተዋቀረው አስመራጭ ኮሚቴ፣ የምርጫ ቦርድ የምርጫ ማካሄጃ የጊዜ ሰሌዳ እንደታወቀ የእጩ ምዝገባ ቀን ከመድረሱ በፊት አስቀድሞ በወረዳው ለመወዳደር ያመለከቱ እጩዎችን ሰብስቦ አጠቃላይ ግንዛቤ አስጨብጧል። ጠቅላላ ጉባኤ ከመጠራቱ ቀድሞ ኮሚቴው የእጩዎቹን ሰነድ ከፍቶ፣ በመስፈርቱ መሠረት ለእያንዳንዳቸው እጩዋች ውጤት ሰጥቷል።

በዚህም መሠረት ከ95/100 እስከ 35/100 ድረስ ውጤት ያገኙ አስራ ሶስት ተወዳዳሪዎች በጽ/ቤቱ በማስታወቂይ ቦርድ ላይ በመለጠፍ አሳውቋል፡፡ ኮሚቴው ከቀረቡለት 16 እጩ አመልካቾች መሀከል አንድ ተወዳዳሪ በሥነ ምግባር ግድፈት በመፈፀማቸውና ሌላ አንድ ተወዳዳሪ የሚጠበቅባቸውን መስፈርት በአግባቡ ባለሟሟላታቸው ኮሚቴው ሰርዟቸዋል። በውጤቱ መሠረት አቤቱታ አቅራቢ እጩ አመልካች ካለ ለወረዳው የዲሲፕሊን ኮሚቴ ይግባኝ የማቅረብ መብታቸውንም አሳውቋል።

ይህ ከተከናወነ በኋላ በሁለት ቀናት ልዩነት ለወረዳው ጠቅላላ ጉባኤ አባላት እጩዎቻቸውን እንዲመርጡ ቀኑን በማሳወቅ ጥሪ አድርጓል። ምርጫ ወረዳው አስቀድሞ በተከራየው አዳራሽ አባላት እንዲገኙ አድርጓል። በዕለቱም ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ጀምሮ የምርጫ እጩ መልማይ ኮሚቴና የምርጫ ወረዳው ሥራ አስፈፃሚዎች ወደ አዳራሽ የሚገቡ አባላት በትክክል የወረዳው አባል መሆናቸውን እያጣሩ እንዲገቡ አድርገዋል፡፡ይህም የሆነበት ጉዳይ ከአባላት ማለትም ከጠቅላላ ጉባኤ አባላት ውጭ ሌሎች ደጋፊ ወይም ሌላ አካላት ድምፅ የመስጠቱን ሒደት ታማኝነት እንዳያሳጡት ለማድረግ ታስቦ የተሠራ ሥራ ነው። በዕለቱ ከተጠሩት 100 የኢዜማ ምርጫ ወረዳ አባላት መሀከል 70 አባላት ሰዓታቸውን አክብረው መገኘታቸው ሲረጋገጥ የዕለቱ ፕሮግራሙ በኢዜማ ሊቀ መንበር በአቶ የሺዋስ አሰፋ የመግቢያ ንግግር ተጀምሯል። በታዛቢነት በማዕከል ደረጃ የምርጫ አደረጃጀት ኃላፊ የሆኑ አመራሮች ተገኝተዋል፡፡ በዕለቱ አንድ የምርጫ አስመራጭ ኮሚቴ አባል በግል ጉዳይ ባይገኙም ቀሪዎቹ የኮሚቴ አባላት በመገኘታቸው የተዘጋጀላቸውን ቦታ ከያዙ በኋላ ዝግጅቱ ተጀምሯል። ዝግጅቱ ከተጀመረ በኋላም ወደ ውስጥ መግባትም ሆነ ወደ ውጭ መውጣት አጥብቆ የተከለከለ መሆኑ በማሳወቅ የተገኙ ጉባኤተኞች ተቆጥረው፣ ሊስት/አቴንዳስ ጋር ተገናዝቦ ልክ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ በቀጥታ ወደ ዋናው ሥነ ሥርዓት ተገብቷል፡፡ የምርጫ ኮሚቴው ሰብሳቢና የወረዳው ሊቀ መንበር የመግቢያ ንግግር ካደረጉ በኋላም የእጩ መልማይ ኮሚቴ ሰብሳቢ የቀረቡለትን የእጩ ዝርዝር ጉዳይችን አንድ በአንድ በማቅረብ ያገኙትን ውጤት በመግለጽ ዕጩዎቹን ለጉባኤው አስተዋውቀዋል።

በዚህም መሠረት እያንዳንዱ እጩ ተመራጭ በኮሚቴው በተሰጠው የአምስት ደቂቃ ጊዜ (እያንዳንዱ እጩ ከተሰጠው አምስት ደቂቃ በላይም መናገር አይችልም) በዋናነት ራሳቸውን ማስተዋወቅ፣ የትምህርት ዝግጅታቸውን፣ የፖለቲካና የማኅበረሰባዊ ተሳትፎቻቸውን፣ ኢዜማን ወክለው ቢመረጡ ለተመረጡለት ማኅበረሰብ ወይም አካባቢ ምን ሊሰሩ እንዳቀዱ አጠር ያለ ማብራሪያ አቅርበዋል፡፡ በዚህ ሂደት የመጀመሪያዎቹ አራት እጩዎች ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለመወዳደር ጉባኤው በድምፅ ብልጫ እንዲመርጣቸው ወደ መድረክ በመውጣት ራሳቸውን ካስተዋወቁ በኋላ እንደ ደረጃቸው ድምፅ ተሰጥቷል። ከፍተኛ የሆነ ድምፅ ያገኙ አንድ እጩ ወረዳውን ወክለው ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እጩ ሆነው ለመወዳደር ከጉባኤው ይሁንታን አግኝተዋል፡፡ በቀጣይ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተወዳድረው በድምፅ ብልጫ ተሸንፈው የቀሩትን ሦስት እጩዎች በፈቃደኝነት ወደ አዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት በቀጥታ ከሌሎች አስር የአዲስ አበባ ምክር ቤት ተወዳዳሪዋች ጋር ለማወዳደር ደንቡ ስለሚፈቅድ በድጋሚ ለከተማው ለምክር ቤት እንዲወዳደሩ ተደርጎ የአዲስ አበባ ምክር ቤት ተወዳዳሪዎች ወደ መድረክ ወጥተው የተሰጣቸውን አምስት ደቂቃ በተለመደው መልኩ ራሳቸውን አስተዋውቀውበታል፡፡

ሴቶች በፖለቲካው መድረክ ያላቸውን ተሳትፎ ለማጎልበት በማሰብ ለአዲስ አበባ ምክር ቤት ለመወዳደር የቀረቡ አንድ የሴት ተወካይ፣ ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በድምፅ ብልጫ ተሸንፋ ወደ ከተማ ምክር ቤት የተሸጋገረች ሌላ አንድ ሴት በመጨመር በድምሩ ሁለት ሴቶች በቀጥታ ለአዲስ አበባ ምክር ቤት ለመወዳደር እጩ ሆነው እንዲያልፉ ተደርጓል።

የቀሩት አስራ አንዱ እጩዎች በድምፅ ብልጫ ተወዳደረው ጠቅላላ ጉባኤው ከፍተኛ ድምፅ የሰጣቸው አራት እጩዋች ተመርጠዋል። በቀጥታ በጠቅላላ ጉባኤው ከተመረጡ ሁለት ሴቶች ጋርም ወረዳውን በአዲስ አበባ ምክር ቤት ስድስት ሆነው እንዲወክሉ ተመርጠዋል፡፡ በአጠቃላይ በወረዳው ለጠቅላላ ጉባኤ ከቀረቡት አስራ አራት እጩዎች መሀል አንድ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ በድምፅ ብልጫ ሁለት በቀጥታ እና አራት በድምፅ ብልጫ በድምሩ ስድስት እጩዎች ለአዲስ አበባ ምክር ቤት ተመርጠው ቃለ መሐላ ፈፅመው በሰላምና ፍጹም ዴሞክራሲያዊ በሆነ ፉክክር ፕሮግራሙ ተጠናቋል።

በዚህ ዘግጅት ላይ የወረዳው ቀበሌ አስተዳደር አዳራሽ በመፍቀድና የወረዳው ፖሊስ ሰላም በማስጠበቅ ከጎናችን ስለነበሩ ምርጫ ወረዳ 28 ምስጋናውን ያቀርባል፡፡


## አድራሻ

ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema

የኢትዮጵያ ዜጎች
ለማኅበራዊ ፍትህ
(ኢዜማ)

ጥር 06 ቀን 20113 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# ነፃ ሀሳብ

ማሳሰቢያ:- ይህ ፅሁፍ የፀሐፊውን አቋም ብቻ ነው የሚወክለው!

የዚህ ፅሁፍ አዘጋጅን ማግኘት ቢያስፈልግ tekleb2006@gmail.com ይጠቀሙ

# የትግራይ ፈተና እና የመቀሌ ቆይታዬ

ተክሌ በቀለ



## እንደ መግቢያ

የ46 አመቱ ድርጅት፣ ሕወሓት ፈርሷል፡፡ ለ30 ዓመታት የገነባው መንግሥታዊ መዋቅርም እንዲሁ ተከስክሷል፡፡ በክልሉም ይሁን በመላ ሀገራችን የተዘረጋው ድር ተበጣጥሷል፤ እየተበጣጠሰም ይገኛል፡፡ አሳዛኝ ክስተትም አስከትሎ ነው ያለፈው፡፡ ባለው ላይ እየጨመርን የተሻለ ሃሳብ በሰላም እያሸነፈ ፤ የሕዝብ ሰላም ሳይታወክ ፤ ህይወት እና ንብረት ሳይወድም የስልጣን ቅብብሎሽ አለያም ከአንዱ ቡድን ወደ ሌላው ሽግግር ቢደረግ መልካም ነበር፡፡ ያ እስከ ዛሬ ድረስ ባለመደረጉ ውድ ዋጋ እንደሃገር ከፍለናል፤ እየከፈልንም እንገኛለን፡፡ ሕወሓት እንደ ፓርቲም ሆነ እንደመንግሥት ቢነቀልም አስተሳሰቡ ገና በህይወት ላይ ይገኛል ብሎ ሚያምን ሕዝብ ብዙ ነው፡፡የአስተሳሰቡ ህያው ምንጭ ሕገ-መንግሥቱ ለመሆኑ የሚከራከሩ ወገኖች ብዙ ናቸው፡፡ የኔም እምነት ይኸው ነው፡፡ በመሆኑም የትግራይ ፈተና ቀጣዩ የሀገራችን ፈተና አንዱ እና ትልቁ ነጥብ ሆኖ ይቀጥላል፡፡ ፈተናውን በጋራ እንደ ሕዝብ እና ሀገር ሆነን ካላለፍነው የህልውናችን ስጋት ሊሆን እንደሚችል መገመት አይከብድም፡፡ ሕወሓት ለማስፈራሪያነት እንዲያገለግል ጨርሶ እንዳይጠፋ የሚፈልግ አካል አይኖርም ብሎ አለማሰብ የዋህነት ሊሆን ይችላል፡፡ ሕወሓት የመረጠችው መንገድ መጠፋፋትን ስለሆነ ሌላ ምርጫ ያልተወችልን መሆኑ ያሳዝናል፡፡ በመሆኑም ለትግራይ ሕዝብ ዘላቂ ሰላም እና ልማት ጭምር በተያዘው ፍጥነት ትግራይ ከመርዙ መፈወስ ይኖርባታል፡፡ በዚች አጭር ፅሁፌም የመቀሌን ሕዝብ ስሜት እና የከተማውን/አካባቢውን ሁኔታ እንዲሁም ቀጣይ ፈተና ሊሆኑብን ስለሚችሉ ጉዳዮች ለመዳሰስ እሞክራለሁ፡፡

## የመቀሌ ቆይታዬ እና የሕዝቡ ስሜት

ከ10 ዓመታት በኋላ ነው ወደ መቀሌ ተጉዤ ለሳምንት ያህል ቆይታ ማድረግ የቻልኩት፡፡ ወደ ገጠሩ አካባቢ ባልወጣም የተወሰኑ ዘመዶቼን ጎብኝቻለሁ፡፡ ከሽረ እስከ ማይጨው ጉብኝት ካደረጉ የተለያዩ የፓርቲ አባላትና ከፍተኛ አመራሮች ጋርም በተደጋጋሚ ተወያይተናል፡፡ በፓርቲ ያልታቀፉ ከድሮ ጀምሮ የሕወሓትን ፖለቲካ ከሚቃወሙ ምሁራን ጋርም ተወያይተናል ፡፡ ከሳምንት በላይ በቆየንበት ግዜ የሕዝቡንም ስሜት ለመረዳት ሞክረናል ፡፡ ኢዜማ፣ ብልፅግና፣ ዓረና፣ ትዴፓ እና ራዴፓ ለግዜው ተሰባሰበው ያለውን አጠቃላይ ሁኔታ ተረድተዋል፡፡ ግጭቱ ሲካሄድም ሆነ ከዚያ በፊት የነበረውን ሁኔታ በአካል የተመለከቱ የየፓርቲዎቹ የክልሉ አመራሮች እና አባላት በአይናቸው ያዩትን ሁሉ መረጃ አካፍለዋል ፡፡ በፓርቲዎች ከሚወጡት መረጃዎች እና አቋሞች በተጨማሪ በግሌ የተገነዘብኩትን በተለያዩ ሚድያዎች እያጋራሁ እገኛለሁ፡፡ ብዙ ነገሮች የተሰሙኝ ቢሆንም ሕወሓት የሌለባትን መቀሌን/ትግራይን ማየት የፈጠረብኝን ስሜት ለመግለፅ ቃላት ▶



▶ ያጥረኛል፡፡ ከላይህ ላይ ከባድ ሸክም የተራገፈልህ ያህል ይቀለሃል፡፡ የታሰረ ህሊናህ ፤ ቂም የቋጠረ ልብህ ፤አቅመ ቢስ ያደረጉት ሃሞትህ በአጠቃለይ የስሜት ህዋሶችህ ሲፍታቱ ይታወቀሃል ፡፡ ህመም ላይ የነበረችው ህይወትህ ስታገግም ይሰማሃል፡፡ ደግሞም ስንት ውድ ዋጋ ተከፍሎ ነፃ እንደወጣች ስታስበው የጀግኖቹ ደም እና ህይወት ፊትህ ላይ ድቅን ይላል፡፡ መሬቱ ግን ምን ቢሆን ነው ሁሌም የሰው ልጅ ደም እና አጥንት የሚጠማው?! ያሳዝናል ፡፡

በዚህ ግጭት ትግራይ እንደ ክልል በጣም ተጎድታለች፡፡ በኔ እምነት ሕወሓት ግጭቱ ትግራይ ውስጥ እንዲካሄድ ከማድረጉም በላይ እሳቱን የለኮሰው ራሱ በመሆኑ የቅድሚያው ተጠያቂና ወንጀለኛ ራሱ ነው፡፡ በዚህ ወንጀል ስር ግን ሌሎች ወንጀል የፈፀሙ ኃይሎች እንዳሉ ሕዝብ እየተናገረ ነው፡፡ በትግራይ ሕዝብ ላይ ተዘምቷል የሚል እምነት አለ፡፡ ሕወሓትን ከሕዝብ ያልለየ ጥቃት ተደርጓል፡፡ የንፁሃን ደም ፈሷል፡፡ ንብረት ወድሟል፤ተዘርፏል፡፡ ቅርስም ወድሟል፡፡ ይህ በትግራይ ሕዝብ ዘንድ የመጠቃት ስሜት ፈጥሯል፡፡ ወደ ቁጨትም እያደገ ይመስላል፡፡ ለዚህ ጥቃት ዋንኛ ተጠያቅው የኤርትራ ታጣቂዎች ሲሆኑ አሁን አሁን የመከላከያችን ከፍተኛ መኮንኖች እና የአካባቢው አዳዲስ ባለስልጣናትም እየገለፁት ያለ እውነት ሁኗል ፡፡

ይህ ጉዳይ በአፋጣኝ በገለልተኛ ሃገር በቀል ድርጅቶች መጠናት እና ለሕዝብ ግልፅ መሆን ይኖርበታል፡፡ የተበደለ ይካሳል፤ የፈረሰ ይሰራል፡፡ የሕዝብ የጉዳት ስሜት የሚታከመው ግን ጥፋተኛው ሲለይ እና በይቅርታም በሕግም ሲደመደም ይሆናል፡፡ ጉዳዩም የትግራይ ሕዝብ ብቻ አይደለም፡፡ የሕዝብ እና ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ጭምር ነው፡፡ ሕዝብን ባለመጠበቅ መንግሥት እና የወቅቱ የፖለቲካ ባለስልጣኖች ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡ መንግሥትም ራሱን ማንፃት ካለበት የደረሰው ጥቃት በገለልተኛ ወገን እንዲጠና ማድረግ ይኖርበታል የሚለው ሃሳብ የበርካታ ወገኖች እምነት ነው ፡፡ ሁሉም ሊረጋጋ የሚችለው ታማኝነት ያለው የገለልተኛ ሪፖርት ሲደመጥ ነው፡፡ የፖለቲካ ፓርቲዎች፤ የታዋቂ ሰዎች፤ የሚድያዎች ዝምታ ሕዝብን ለባይተዋርነት እየዳረገ ይመስላል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ተገቢው ማጣራት እንዲካሄድ ኢዜማ እንደፓርቲ እየወተወተ ይገኛል፡፡ ውትወታው ትክክልም ይመስለኛል፡፡ መከላከያ ጥቃት ተፈፅሞበት ሕግን ለማስከበርና ራሱን ለመከላከል ውጊያ እያካሄደ ሀገር ሊያስተዳድር አይቻለውም፡፡ ትግራይ ሰፊ አካባቢ በመሆኑ ሁሉን አካባቢ ሸፍኖ ጥበቃ ሊያደርግ የሚቻለው ላይሆን ይችላል፡፡ መጠኑ በጣም ቢቀንስ እንጂ ዛሬም ግጭቱ ጨርሶ አልቆመም ፡፡ ሰላም እና ፀጥታው በሚፈለገው ፍጥነት እየተመለሰ አይመስልም፡፡

‹‹ በ1967/68 ነው አሉ፡፡ ሽረ ከተማን የኢድዩ፣ የሕወሓት እና የኢትዮጵያ የመንግሥት ወታደሮች በፈረቃ ይይዟት ነበር ፡፡ እናቶች በፍርሃት ጧት ላይ ሕወሓት ከገባች እልልታውን ያቀልጡታል፡፡ ከሰዓት በኋላ የመንግሥት ወታደሮች ካስለቀቁ እና ከገቡ እንዲሁ እልልታዉን ያቀልጣሉ፡፡ ወደ ማታ ኢድዩ ከገባም እንዲሁ ያደርጋሉ ፡፡››

በግጭት አለያም በጦርነት ወቅት ዘራፊ እና ጉዳይ ከውስጥም ከውጪም ሊመጣ ይችላል ፡፡ እዚህ ላይ አንድ ታዋቂ ምሁር በግዜው በወጣትነቱ የታዘበውን እና ያጫወተኝን እንድጠቅስ ይፈቀድልኝ፡፡ በ1967/68 ነው አሉ፡፡ ሽረ ከተማን የኢድዩ፣ የሕወሓት እና የኢትዮጵያ የመንግሥት ወታደሮች በፈረቃ ይይዟት ነበር ፡፡ እናቶች በፍርሃት ጧት ላይ ሕወሓት ከገባች እልልታውን ያቀልጡታል፡፡ ከሰዓት በኋላ የመንግሥት ወታደሮች ካስለቀቁ እና ከገቡ እንዲሁ እልልታዉን ያቀልጣሉ፡፡ ወደ ማታ ኢድዩ ከገባም እንዲሁ ያደርጋሉ ፡፡ በአንድ ቀን ውስጥ ለሶስት ቡድን ጦረኞች በፍርሀት እልልታ ያሰማሉ፡፡ የሚገርመው ነገር አንዱ ቡድን ገብቶ በሌላኛው እንዲለቅ ሲደረግ በመሃል ከተማው ያለ አስተዳደር ባዶ የሚሆንበት ግዜ ነበር አሉ ፡፡ በዚህ ግዜ እቃ ለመዝረፍ የአካባቢው የገጠር ሰው አህያ ጭኖ ወደ ከተማው በመግባት ከተሜውን ያጠቃ ነበር አሉ፡፡ ዛሬም መቀሌን ጨምሮ ከተሞች በትግራይ እየተዘረፉ፤ እየተጠቁ ሰውም እየተገደለ ይገኛል፡፡ በቀላሉ ልንገልፀው የማይቻለን ግፍ ተፈፅሟል፡፡ የዚህ ግጭት ዘራፊዎች ድንበር ጥሰው፤ በአህያ ሳይሆን በመኪና ጭነው የሚሄዱ መሆናቸው ጉዳዩን ከባድ ያደርገዋል፡፡

ሕወሓት ይህን ለማስባል ተንኮሉ ያንሰዋል ተብሎ አይታሰብም፡፡ ሕወሓት የመከላከያን ሆነ የሻዕቢያን ዩኒፎርም አልብሳ አትዘርፍም፤ አታዘርፍም ማለት አይቻልም፡፡ ሁሉም የሚመቸውን ለማለት የሚቻልበት ሁኔታ ተፈጥሯልና የማጣራቱ ስራ ተገቢ ይሆናል፡፡ የሚጠራው ግን በገለልተኛ ወገን ሲታይና ሪፖርት ሲደመጥ ይሆናል፡፡

መቀሌን ጨምሮ ደቡባዊው የትግራይ ክፍል ከቀን ወደ ቀን እየተረጋጋ ▶

ነው፡፡ ለእንደርታም ሆነ ለሌላው የትግራይ ሕዝብ ነገም ሌላ ብሩህ ቀን ነው፡፡ ብሩህ ዘመን ነው፡፡ ሰውን ከነ ክብሩ ማሸነፍ ትልቅነት ነው፡፡ ምናልባት ከነሱ የከፋት ጥግ አኳያ ሲታይ አልተሳካልን ይሆናል፡፡ ክብራቸው ተዋርዶም ቢሆን ተሸንፈዋል፡፡ የሆነው ሆኖ ትናንት በግድ እንዲመርጥ የተገደደው ሕዝብ፤ ለ46 ዓመታት የተጫነው ድርጅት ከጫንቃው ወርዷል፡፡ እንደ እሩቅ ዘመድ፤ ሞቶ እንደቀበረው፤ አፈር እና ድንጋይ እንደጫነበት ሬሳ አፈር በትኖ እርሙንም አውጥቶ ረስቶታል፡፡ እንደዘበት መንግሥት ሄዶ መንግሥት፤ ፓርቲም አልፎ ፓርቲ እየመጣ ነው፡፡ «አብሮ የበላ አብሮ ይሞታል» እንዲሉ ጥቂት ተጠቃሚዎች አለያም የዘረኝነት ሰበካው አጥንታቸው ድረስ የዘለቀ እዚህም እዚያም ሲያንጎራጉሩ እንሰማ ይሆናል ፡፡

## የጊዜያዊ አስተዳደሩ/የመንግሥት ችግሮች

የሕወሓትን እንደ መንግሥት እና ድርጅት መፍረስ ተከትሎ በአዋጅ ቁጥር 350/1995 መሰረት ጊዜያዊ አስተዳደር በትግራይ እንዲቋቋም መንግሥት መወሰኑ ይታወሳል፡፡ የጊዜያዊ መንግሥቱ ዋና ስራ አስፈፃሚም ከላይ እስከታች ጊዜያዊ አስተዳደር እያዋቀረ ይገኛል፡፡ ክልሉ እንዲረጋጋ፤ሀገራችን ሰላም እንዲሆን በፍጥነት ጊዜያዊ አስተዳደር መዋቀሩ ተገቢ ነው፤ ሁሉም ሊያግዘውም ይገባል፡፡

ጊዜያዊ አስተዳደሩ ለታዋቂ ሰዎች፤ ለምሁራንና በክልሉ ለሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች የመዋቅሩ አካል እንዲሆኑ ጥሪ ማስተላለፉ ይታወሳል፡፡ ኢዜማ ስለትግራይና ሕወሓት ጉዳይ በተደጋጋሚ እየተወያየ አቋም እየያዘ የመጣ ፓርቲ እንደመሆኑ በፌደራል እና በክልል ያለውን ሁኔታ የሚከታተሉ አመራሮችን መድቧል፡፡ በቅርበት የክልሉን ሁኔታ እንደሚከታተል አካል ሕግ በማስከበር ዘመቻውና ይህን ዘመቻ ተከትሎ ባለው ግዜ ውስጥ እየተከሰቱ ያሉና ሊከሰቱ ይችላሉ ተብለው የሚነሱ ጉዳዮች ማየቱ ተገቢ ይሆናል ፡፡

የጊዜያዊ አስተዳደሩ የሹመት አሰጣጥና መዋቅሮችን መልሶ የማስተካከል ጉዳይ የግልፅነት ችግር ይታይበታል የሚል የብዙዎች እሳቤ እየሆነ ይመስላል፡፡ በዚህ መሃል ደግሞ የተለያዩ ፍላጎቶች ያሏቸው ግለሰቦችና ቡድኖች እንዲሁም የፈራረሰው የሕወሓት መዋቅር ሰርገው የማይገቡበት ሁኔታ አይኖርም ተብሎ አይታሰብም፡፡ በዚያ ላይ የሕወሓትን የጠነከረና የፈረጠመ ድርጅታዊ እና መንግሥታዊ አስተዳደርን ለለመደ ሕዝብና ቢሮክራሲ አሁን ያለው ከዚህም ከዚያም የሚደረት ጊዜያዊ አስተዳደር ይመጥነዋል ለማለት ያስቸግራል፡፡ ጊዜያዊ ቢሆንም የተሸከመው ኃላፊነትና በስልጣን ላይ ራሱን ያገኘበት ሁኔታ እጅግ ውስብስብ ያደርገዋል፡፡ ለዚህም ነው ከፌደራል ተቋማት እና ከሁሉም ወገኖች እገዛ ያስፈልገዋል የሚባለው፡፡

ከላይ ለመጥቀስ የሞከርኩት የሕዝቡ የመጠቃት ስሜት ከፍተኛ ነው፡፡ ዛሬም ድረስ መከላከያው ሙሉ ሰላሙን እያስጠበቀለት ባለመሆኑ ቅሬታ እያሳደረ መሆኑን ብዙዎች ይገልፁታል ፡፡ በክልሉ ታጥቆ ከሚንቀሳቀሰው የኤርትራ መንግሥት ታጣቂዎች ጥቃት ሙሉ ለሙሉ ሊታደገው አልተቻለውም፡፡ በዚህ ሳቢያ ቂም እና ኩርፊያ እየበዛ ነው፡፡ በዚህ ወቅት የሚያስጨንቀው የትግራይ ሕዝብ መረጋጋት እንጂ የፖለቲካው ጨዋታ መሆን የለበትም ፡፡ የትግራይ ሕዝብ አሁን ካለበት ችግር ተላቆ ነገ ከነገ ወድያ መሪዎቹን መምረጥ እንዲችል መታገል የወቅቱ የሀገር ወዳድ ሰዎች ትልቁ ትግል መሆን ይኖርበታል፡፡

የኢፈርት ጉዳይም እንደነበረው በክልሉ መንግሥት ቁጥጥር ስር አድርጎ ካልሰራ ወደ ኢኮኖሚው ካልተመለሰ አንዱ ትልቁ ችግር ይሆንበታል፡፡ በግጭቱ ወድሞ እና በህይወት እያሉም ቢሆን ቀፎው የቀረ ድርጅት እንደሆነ መገመት ቢቻልም ሌሎች የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች የነበሩት ተመሳሳይ ተቋማት ሳይነኩ ለኢፈርት ብቻ የሚወጣ አዲስ አሰራር ትክክል ስለማይሆን በክልሉ ሌላው የአስተዳደሩ ችግር መሆኑ አይቀርም፡፡ በዚያ ላይ የኢፈርት አባላት የሆኑ ድርጅቶችም ሆነ ሌሎች የግል ተሸከርካሪዎች በመከላከያ ታግተዋል አለያም ተማርከዋል ተብለዋል፡፡ ግጭቱ ሕግን የማስከበር እንጂ በሁለት ወገኖች የተደረገ ጦርነት አለመሆኑን መንግሥት በተደጋጋሚ ማሳወቁ ይታወቃል ፡፡ ከዚህም አልፎ የግል እና የመንግሥት ተሽከርካሪዎች በታጠቁት የኤርትራ ሃይሎች መዘረፋቸውን ብዙ ወገኖች እያጣቀሱ ይናገራሉ፡፡

ይህ በአገልግሎቶች ላይ ተፅእኖ ከማሳደሩም በላይ የመዘረፍ ስሜትን ስለሚያስከትል በክልሉ መንግሥት መረጋጋት ላይ ጫና ማሳደሩ አይቀርም፡፡ ከወዲሁም እያሳደረ ይገኛል፡፡

መልሶ ማቋቋምና የመሰረተ ልማት ግንባታ ሌላኛው ፈተና ሆኖ ይገኛል፡፡ በመንግሥት ሚድያዎች የሚነገረውን ያህል ባይሆንም መልካም ጅማሮዎች አሉ፡፡ የተፈጠረው ሰብዓዊ ቀውስ ከባድ በመሆኑ በፍጥነት ካልተሰራበት ለጊዜያዊ አስተዳደሩ ሌላው ፈተና ይሆናል፡፡ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የመንግሥት ሠራተኛ፣ የኢፈርት እና ሌሎች የግል ኩባንያ ሠራተኞች ደሞዝ ካገኙ ቆይተዋል፡፡ ድርጅቶቹ ሥራ ባለመጀመራቸው ተጨማሪ ኢኮኖሚያዊ እና ሰብዓዊ ቀውስ ተፈጥሯል፡፡ አንዱና ከፍተኛ የመንግሥት ችግር ከመሆኑም አልፎ የደህንነት ስጋትም ይሆናል፡፡

ማጠቃለያ

ጊዜያዊ አስተዳደሩ ሌሎች በርካታ ችግሮች ከፊቱ ሊጠብቁት እንደሚችሉ ይታመናል፡፡ የፈረሰ መዋቅርን መልሶ መገንባትና ማዋቀር ከባድ ሲሆን የሕዝብን ስነ-ልቦና መመለስ ደግሞ ችግሩን የበለጠ ውስበስብ ያደርገዋል፡፡ በመሆኑም ሁሉም ሊያግዘው ይገባል፡፡ ከፕሮፖጋንዳ ይልቅ መሬት ላይ የሚታይ ሥራን ሕዝብ ይመርጣል፡፡ ሕዝቡ ውሸት ሰልችቶታል፡፡ እናም በሰከነ መንፈስ ማወያየትን፤ አቅም በፈቀደ መጠን በፍጥነት ለችግሮች መፍትሄ መስጠትን ከመንግሥት ይጠብቃል፡፡ በዚህ ወቅት ሀገር ወዳድ ሁሉ ከትግራይ ሕዝብ ጎን በመቆም ታሪካዊ ግዴታውን ሊወጣ ይገባል ፡፡ በቀላል ስህተቶች ለመርዘኛ ዘረኞች ዳግም እድል ሊሰጣቸው አይገባም፡፡





# በግብርናና ከተፈጥሮ ኃብት ልማት ዙሪያ የተዘጋጁ ስምንት ፖሊሲዎች ለውይይት ሊቀርቡ ነው

ጥር 6 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በያዝነው ዓመት ግንቦት መጨረሻ ለሚደረገው ሀገር አቀፉ ምርጫ የአገራችንን ችግሮች በሂደት ይፈቱልኛል፤ ዜጎች የተሟላ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ባለቤትና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያስችላሉ፤ ሁለንተናዊ፣ መሰረተ ሰፊና ሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍል በየደረጃው ተጠቃሚ የሚያደርግ የምጣኔ ኃብት ዕድገትና ልማት ለማምጣት ይረዳሉ፤ ማኅበራዊ ፍትህ ለማስፈን፤ ዘላቂ ልማትና ዋስትና ያለው ሰላም ለማረጋገጥ፣ እንደዚሁም ዴሞክራሲያዊ ሥርዓተ-መንግሥትን በኢትዮጵያ ዕውን ለማድረግ ይረዳሉ ብሎ ያመነባቸውን 45 የፖሊሲ ሰነዶችና በሂደትም ፖሊሲዎቹን ለማስፈፀም የሚረዱ ስልቶች (strategies) ቀረፃ እያደረገ እንዳለ ይታወቃል፡፡



ፓርቲው እነዚህን ፖሊሲዎች ለባለድርሻ አካላት ይፋ በማድረግ ሂደት ላይ የሚገኝ ሲሆን ከታህሳስ 4 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ በተደረጉ አውደጥናቶች 18 ያህል ፖሊሲዎችን ለውይይት በማቅረብ ግብአት መሰብሰብ ችሏል፡፡ በሚመጡት ሳምንታትም በግብርናና ተፈጥሮ ኃብት ልማት ዙሪያ የተዘጋጁ ስምንት ፖሊሲዎችን ለውይይት እንደሚቀርቡ የኢዜማ የብሔራዊ ፖሊሲ ዝግጅት አስተባባሪ አማን ይኹን ረዳ፣ ለዜጎች መድረክ ገልጸዋል፡፡ ከባለድርሻዎች ጋር ምክክር የሚደረግባቸው ፖሊሲዎች የግብርና ፖሊሲ፣ የገጠር ልማት ፖሊሲ፣ የመሬት ፖሊሲ፣ ምግብ ዋስትናና የሥርዓተ-መብል ፖሊሲ፣ የአደጋ ቅነሳና አስተዳደር ፖሊሲ፣ የአርብቶ አደር ልማት ፖሊሲ፣ የውሀ ኃብት ልማት ፖሊሲ፣ የኢነርጂ ፖሊሲ እንደሆኑ የብሔራዊ ፖሊሲ ዝግጅት አስተባባሪው ለዜጎች መድረክ አስረድተዋል፡፡

ኢዜማ በፖለቲካ፣ በማኅበራዊና በምጣኔ ሀብት ዘርፍ ፖሊሲዎቹን የከፋፈለ ሲሆን በእነዚህ ዘርፎች ሥርም ከ40 በላይ ፖሊሲዎችን የፓርቲው አባል በሆኑና አባል ባልሆኑ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ-ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎችን አሳታፊ ባደረገ መልኩ መቅረፅ ችሏል፡፡ ኢዜማ በማህበራዊ ዘርፍ በሚቀርፃቸው ፖሊሲዎች የድህነትና አለእኩልነት (poverty & inequality) ምንጭ የሆኑትን ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ምክንያቶች በመቀነስ፤ ብሎም ከምንጫቸው በማድረቅ የኢትዮጵያውያንን ኑሮ ለማሻሻል ይሰራል። ፖሊሲዎች ዜጎች የዕኩል መብት፣ የዕኩል ዕድልና የዕኩል አያያዝ (equal right, equal opportunity, & equal treatment) ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማስቻል ከድህነትና አለእኩልነት የተላቀቀ፤ እንደዚሁም ከስጋት ነፃ የሆነና ተረጋግቶ የሚኖር፤ በአካባቢያዊና አገራዊ የምጣኔ ሀብትና ማኅበረ-ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ በንቃት የሚሳተፍና በተሳትፎውና ጥረቱ ልክ ተጠቃሚ የሚሆን ማኅበረሰብ መፍጠርን ግብ ያደረጉ ናቸው፡፡ የኢዜማ የምጣኔ ሀብት ዘርፍ ፖሊሲዎች ፈጣን፣ መሰረተ-ሰፊና የሀገሪቷን ሕዝቦች በየደረጃው ተጠቃሚ የሚያደርግ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማስመዝገብ የሚተገበሩ ዝርዝር ፖሊሲዎች ናቸው። ውጤታማ ፖሊሲዎችን በመተግበር የሥራ አጥ ቁጥር እንዲቀንስና በግል ስንፍና ካልሆነ በስተቀር ዕድሜው ለሥራ የደረሰ ኢትዮጵያዊ ሁሉ አማራጭ ከማጣት የተነሳ ስደት ውስጥ መግባት ሳያስፈልግ በቂ የሥራ ዕድል በአገር ቤት የሚመቻቸበት፤ የተረጋጋ የገበያ ስርዓት በተለይም የመሰረታዊ ፍጆታ ሸቀጦች ዋጋ ከግሽበትም ሆነ ከንረት የፀዳ እንዲሆንና የዳበረ አገር-በቀል የግል ክፍለ-ኢኮኖሚ ዕውን የሚሆንበት ሥርዓት መዘርጋትን ግብ ያደረጉ ፖሊሲዎች እየተዘጋጁ ነው። በኢኮኖሚው ዘርፍ በሚሰራ ውጤታማ የፖሊሲ ቀረፃና አተገባበር የኅብረተሰቡን መሰረታዊ ፍጆታዎች በሐገር ውስጥ በማምረት የኑሮ ውድነትን መቀነስ እንደሚቻል ፓርቲው በፖሊሲዎቹ አመላክቷል፡፡

በፖለቲካው ዘርፍ ያሉት ፖሊሲዎች በኢትዮጵያ የመድብለ-ፓርቲ ሥርዓት እንዲጠናከር፣ የመገናኛ ብዙኃንና ሲቪል ማኅበራት እንቅስቃሴ እንዲጎለብት፤ የፌደራል ሥርዓታችን እንዲዳብርና የዜጎችን ሰብዓዊ መብቶችና ደህንነት ሙሉ ለሙሉ ለማክበር በሚያስችልና ልማትንና አስተዳደርን በሚያቀላጥፍ መልኩ እንዲደራጅ ለማድረግ፤ ሥልጣን ወደታችኛው እርከን የሚወርድበትና ያልተማከለ አስተዳደር በትክክልም ተግባራዊ የሚሆንበትን እውነተኛ ፌደራላዊ ስርዓት እንዲፈጠር የሚተገበሩ ፖሊሲዎች ናቸው። ፖሊሲዎቹ የሕግ የበላይነት እንዲሰፍን፣ የፍርድ ቤቶች ነፃነት፣ የአገር ሰላምና የግዛት አንድነት የሚረጋገጥበት እና ሕዝቡ የሉዓላዊ የስልጣን ባለቤትነቱ ዋስትና የሚያገኝበትን ግብ የሚያሳኩ ናቸው፡፡ በዚህ ዘርፍ በሚተገበሩት ፖሊሲዎች የፖለቲካ ምህዳሩን በማስፋትና የመንግሥትን ስልጣን ሕገ-መንግሥታዊና በሕግ የተገደበ በማድረግ ዜጎች በነቃ ተሳትፏቸው ዕውን የሚያደርጉት ሲሆን ይህም የአገሪቱ የሕዝባዊ-መንግሥት ምስረታ ጥያቄን ለመመለስ የተደረገው የ50 ዓመት ትግል ለማሳካትን እንደ ግብ የያዙ ፖሊሲዎች ናቸው፡፡

በሁሉም ዘርፍ ግብአት ሲሰበሰብባቸውና ሲቀረፁ የቆዩት ፖሊሲዎች፣ የኢዜማ ኮንፍረንስ ካፀደቃቸው በኋላ ለሕዝብ ይፋ የሚሆኑ ይሆናል፡፡

# ኢዜማ፣ ችግር ወደተፈጠረባቸውና ፀጥታ በደፈረሰባቸው አካባቢዎች በከፍተኛ አመራሮች የሚመራ ቡድን እንደሚልክ አስታወቀ

ጥር 6 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በያዝነው ዓመት የሚካሄደው ሀገር አቀፍ ምርጫ ሀገሪቷ ያለችበትን አስቸጋሪና አደገኛ ሁኔታ ወደ የተሻለ የተረጋጋ ሀገራዊ ሁኔታ ከመቀየርና በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚሞከረው የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደትን ጥሩ ከማድረግ አንጻር ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ አለው ሲል አስታወቀ፡፡

ኢዜማ ሀሙስ ጥር 06 ቀን 2013 ዓ.ም በዋና ጽህፈት ቤቱ በመስፍን ወልደማሪያም አዳራሽ፣ ለመገናኛ ብዙኃን በወቅታዊ ጉዳዮች እና በምርጫ 2013 ዙሪያ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ምርጫው አለው ያለውን ታሪካዊ ጥቅም በዝርዝር አቅርቧል፡፡ የ2013 ምርጫ ተቀባይነት ባለው ሂደትና ውጤት ሊጠናቀቅ የሚችልበት እድል መኖሩ፣ ሀገሪቷ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ የሕዝብ የምርጫ ፍላጎት ተግባራዊ ሊሆን የሚችልበት እድል መኖሩ፣ በሀገሪቱ የሚገኙ ሀገራዊና ክልላዊ ፓርቲዎች፣ ከሕዝብ ሊኖራቸው የሚችለውን ድጋፍ በሠለጠነ የምርጫ ሂደት ውጤት ማወቅ የሚችሉበት ጥሩ ታሪካዊ አጋጣሚ ሊኖር መቻሉ፣ ለወደፊት ለሚደረጉ ምርጫዎች ተጨባጭ ልምዶች ማግኘትና ልምዶቹን በመጠቀም የተሻለ ምርጫ ማድረግ የሚቻልበት መልካም አጋጣሚ መሆኑ፣ በምርጫ አሸናፊ የሚወጣው ድርጅት ከዚህ በፊት ከነበሩት መንግሥታት በሙሉ ሕጋዊ ቅቡልነት ያለው አካል ሊሆን የሚችልበትም አጋጣሚ መፍጠሩ፣ ተቀባይነት ያለው የምርጫ ሂደትና ውጤት መሰረት አደርጎ የሚቋቋመው መንግሥት፣ በኢትዮጵያ ጥቅምና ደህንነትን በሚመለከት ከማናቸውም ሦስተኛ አካል ጋር የሚያደርገውን ስምምነትም ሆነ ውል፣ ከሕጋዊ ቅቡልነት የሚመነጭ፣ ጠንካራ አቅም ሊያገኝ የሚችልበትን ዕድል መፍጠር መቻሉ የቀጣዩ ምርጫ ፋይዳን ከፍተኛ ያደርገዋል ሲል ኢዜማ በመግለጫው አመላክቷል፡፡

ፓርቲው ከፍተኛ ፋይዳ አለው ላለው ምርጫ ሲያደርግ የቆየውን ዝግጅት በመግለጫው ላይ በዝርዝር ጠቅሷል፡፡ ኢዜማ ካስቀመጣቸው አራት ስትራቴጂያዊ ግቦች አንዱ በምርጫ አሸንፎ መንግሥት መሆን የሚል መሆኑን አስታውሶ፤ ይሄንን ስትራቴጂያዊ ግብ እና የፓርቲ ውስጠ ዴሞክራሲን ያሳካል ብሎ ያመነበትን አደረጃጀት ሲዘረጋ መቆየቱን ገልጿል። የፓርቲው የምርጫ ዘመቻ በብሔራዊ፣ በክልል እና በወረዳ ደረጃ በሶስት ክፍል የተከፈለ መሆኑን የጠቆመው ኢዜማ፣ በብሔራዊ ደረጃ ለምርጫ ዘመቻ የሚረዳ የምርጫ ስትራቴጂ ማኔጅመንት ኮሚቴ ተዋቅሮ እየሠራ እንደሚገኝ ጠቅሷል፡፡ ይህ ኮሚቴ በዕጩ ምልመላ እና ድጋፍ፣ በፖሊሲ እና ማኒፌስቶ ዝግጅት፣ በድርጅት አቅም ግንባታ እንዲሁም በሐብት አሰባሰብ ዙሪያ በስፋት እየሠራ እንደሚገኝ የገለፀው ኢዜማ፣ በክልልና በምርጫ ወረዳ ላይ ያሉ የዘመቻ ክፍሎች በማዋቀር ላይ እንደሚገኝ ጠቁሟል ፡፡

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትም ሆነ በክልል ምክር ቤት የሚወዳደሩ ዕጩዎችን በማስመረጥ ላይ እንደሆነ የገለፀው ኢዜማ እስከ ጥር 16 ቀን 2013 ዓ.ም ድረስ ሁሉም ዕጩዎች በየምርጫ ወረዳው ተመርጠው እንደሚታወቁ አሳውቋል፡፡ ከጥር 1 ቀን ጀምሮ የምርጫ ወረዳዎች ጉባዔ በማድረግ ቀደም ብሎ በተዘጋጀ የዕጩ መለያ መመዘኛ መሰረት ኢዜማን ወክለው በምርጫ ለመወዳደር ፍላጎት ኖሯቸው ካመለከቱ አባላት ምዘናውን በከፍተኛ ውጤት ያሚሉትን የመጨረሻ ውድድር በማድረግ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና ለክልል ምክር ቤቶች የሚወከሏቸውን ዕጩዎች እየመረጡ እንደሚገኙ ያስታወሰው ፓርቲው፣ ሂደቱ በፓርቲ ውስጠ ዴሞክራሲያዊ ባሕልን ለመገንባት እና የዴሞክራሲ ባሕል ልምምድ በሀገር ደረጃ እንዲያድግ ትልቅ አስተዋፅኦ ያደርጋል ብሎ እንደሚያምን ገልጿል።

ከመጪው ሀገራዊ ምርጫ ጋር በተያያዘ ኢዜማ ከፍተኛ ዝግጅት ሲያደርግበት ከቆየባቸው ዘርፎች መሀከል የፖሊሲ አማራጭ ዝግጅት ሌላኛው መስክ መሆኑን በመግለጫው ላይ ያወሳው ኢዜማ፣ ፖሊሲዎቹ የኅብረተሰቡን ቁልፍ ችግር በሚፈቱ ዘርፎች በሙያው የላቀ ብቃት እና ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች የተቀረጹ መሆናቸውንና ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው እና በየዘርፉ ላይ ሙያተኛ የሆኑ የፓርቲው አባል ላልሆኑ ኢትዮጵያውያን ጭምር አቅርቦ ያገኘውን ግብረመልስ በመጠቀም ፖሊሲዎቹን በማዳበር ላይ እንደሚገኝ አስታውቋል፡፡

በእስከአሁኑ ሂደትም በ18 የፖሊሲ ሰነዶች ላይ ምክክር ማድረግ መቻሉንና በቀጣይ ቀናት የቀሩትን የፖሊሲ ሰነዶች ለውይይት የሚያቀርብ መሆኑን ጠቁሟል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የምርጫ 2013 ማኒፌስቶ ዝግጅት እየተደረገ እንደሚገኝና በተለያየ ዘርፍ የተዘጋጁትን ፖሊሲዎች እና ኢዜማ ተመርጦ ሥልጣን ቢይዝ በሚቀጥሉት 5 ዓመታት ሊተገብራቸው ቃል የሚገባውን ተግባሮች ዝርዝር የያዘ ማኒፌስቶ ከምርጫው በፊት ለሕዝብ በስፋት የሚያስተዋውቅ መሆኑን ገልጿል፡፡

ኢዜማ በዚሁ መግለጫው ምርጫው ያለው አጠቃላይ ፋይዳ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ይኖራዋል ያለውን ነጥብ ጠቅሷል፡፡ የተወሰኑ ፓርቲዎች መሪዎቻቸው እና አባሎቻቸው በሕግ ጥላ ስር ከመሆናቸው የተነሳ በመጪው ሀገራዊ ምርጫ ሊሳተፉ እንደማይችሉ እየገለፁ መገኘታቸውን በማውሳት፣ የፓርቲዎቹ በመጪው ምርጫ አለመሳተፍ የመጪውን ምርጫ ልዩ ከሚያደርጉት ምክንያቶች አንዱ የሆነውን የሁሉንም ዓይነት አስተሳሰቦች በምርጫው ለውድድር የመቅረባቸውን ዕድል ስለሚቀንስ ምርጫው ያለው አጠቃላይ ፋይዳ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል ብሎ እንደሚሰጋ ገልጿል፡፡

ኢዜማ ችግር ወደተፈጠረባቸውና ፀጥታ በደፈረሰባቸው አካባቢዎች በከፍተኛ አመራሮች የሚመራ ቡድን የሚልክ መሆኑን በመግለጫው የጠቆመ ሲሆን፣ በአካባቢው ያለውን ሁኔታ በመመርመር እና ነዋሪዎችን በማነጋገር ችግሮቹን በተመለከተ ቡድኑ የሚደርስበትን መደምደሚያ ለሕዝብ ይፋ እንደሚያደርግ አሳውቋል፡፡ ኮንሶ፣ መቀሌና መተከል በከፍተኛ አመራሩ የሚመራው ቡድን የሚያቀናባቸው ቦታዎች መሆኑን ዜጎች መድረክ ማወቅ ችላለች፡፡

‹‹የሰላም መደፈረስ በሚታይባቸው የሀገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ ዜጎች በነፃነት በመደራጀት፣ በመሰብሰብና በመንቀሳቀስ እንዲሁም ሀገራዊ፣ ክልላዊና አካባቢዊ መረጃዎችን በመለዋወጥ፤ ፖለቲካዊ አሳባቸውንና አቋማቸውን በማሰማት እውነተኛ ወኪሎቻቸውን በነፃነት የመምረጥን ዕድል አለማግኘታቸው ያሳስበኛል›› ያለው ፓርቲው፣ መንግሥት የጀመረውን የሕግ ማስከበር ተልዕኮ በማፋጠን በእነዚህና በሌሎችም አካባቢዎች ዜጎች ከፍርሃትና ከተስፋ ማጣት ተላቀው እውነተኛ ወኪሎቻቸውን በነፃነት በመምረጥ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ተሳታፊነታቸው ሊረጋገጥላቸው ይገባል ብሎ እንደሚያምን ገልጿል፡፡

# የደብረ ብርሀን ምርጫ ወረዳ የአፈፃፀም ሪፖርቱን አቀረበ

ጥር 6 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የደብረ ብርሃን ምርጫ ወረዳ እሁድ ጥር 02 ቀን 2013 ዓ.ም በደብረ ብርሃን ከተማ ከማዕከል ከመጡ እንግዶች ጋር ውይይት ማድረግ መቻሉን የኢዜማ የደብረ ብርሃን ምርጫ ወረዳ ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ቤተ ማሪያም ብርሃኑ ለዜጎች መድረክ ገለጹ፡፡ የውይይቱ አብይ አላማ የዞኑን እንቅስቃሴ ለመቃኘትና የሥራ አመራር ለመስጠት መሆኑን የጠቀሱት ኃላፊው፣ በዕለቱ ዞኑ የአፈፃፀም ሪፖርቱን ማቅረብ መቻሉንም ጠቁመዋል፡፡ በውይይቱ ላይ የኢዜማ ምክትል ሊቀመንበር ጫኔ ከበደ (ዶ/ር)፣ የኢዜማ የሰሜን ቀጠና አስተባባሪ የሆኑት መለሰ ላቀውና የዕለቱ የክብር እንግዳ የሆኑት በዛብህ ደምሴ (ዶ/ር) ተገኝተዋል፡፡

የኢዜማ ምክትል ሊቀመንበር ጫኔ ከበደ (ዶ/ር) አጠቃላይ የሥራ አመራር አቅጣጫ ለምርጫ ወረዳው መስጠት መቻላቸውን የምርጫ ወረዳው ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ቤተ ማሪያም ብርሃኑ ለዜጎች መድረክ ገልጸዋል፡፡ ከተሳታፊው ለተነሳላቸው ጥያቄዎችም በቂ ማብራሪያ መስጠት መቻላቸውን ጠቁመዋል ፡፡

የእለቱ የክብር እንግዳ የነበሩት በዛብህ ደምሴ (ዶ/ር) ለዞኑ ማስተባበሪያ የሚሆን የ 1 ዓመት የቢሮ ኪራይ ለመክፈል ቃል የገቡ ሲሆን፣ የኢዜማ ምክትል ሊቀመንበር ጫኔ ከበደ አንድ ፕሪንተር፣ ኮምፒውተርና የ30ሺህ ብር የገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ ቃል ሲገቡ፣ የኢዜማ የሰሜን ቀጠና አስተባባሪ የሆኑት መለስ ላቀው ለቅስቀሳ ሥራ የሚውል ሜጋ ፎን ለማበርከት ቃል መግባታቸውን ዜጎች መድረክ ከደረሳት መረጃ ለመረዳት ችላለች፡፡

# ኢዜማ ዕጩዎቹን ማስመረጥ ጀመረ

ጥር 6 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) 6ኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ ላይ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትም ሆነ ለክልል ምክር ቤት ወክለውት የሚወዳደሩ ዕጩዎችን ማስመረጥ መጀመሩን የኢዜማ ድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ዋሲሁን ተስፋዬ ለዜጎች መድረክ ገለጹ፡፡

ቅዳሜ ጥር 01 ቀን 2013 ዓ.ም እና እሁድ ጥር 02 ቀን 2013 ዓ.ም በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ዕጩዎች ማስመረጥ መጀመራቸውን የገለጹት ኃላፊው፣ ዕጩዎቻቸውን ያላስመረጡ ምርጫ ወረዳዎችም የፊታችን ቅዳሜ ጥር 08 ቀን 2013 ዓ.ም እና እሁድ ጥር 09 ቀን 2013 ዓ.ም ዕጩዎቻቸውን የሚያስመርጡ መሆናቸውን የጠቆሙት ኃላፊው፣ ሁሉም ዕጩዎችም እስከ ጥር 16 ቀን 2013 ዓ.ም ድረስ እንደሚታወቁ አስረድተዋል፡፡

ምርጫው ከተካሄደባቸው አካባቢዎች መካከል ምስራቅ ጎጃም፣ ባህር ዳር፣ ደቡብ ወሎ፣ ዳውሮ፣ ኮንታ ልዩ ዞን፣ ሚዛን፣ ቤንቺ ማጂ ዞን፣ ከፋ፣ ሲዳማ፣ ደቡብ ጎንደር፣ ሰሜን ጎንደር ይገኙበታል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት አካባቢዎች ላይ ዕጩዎቻቸውን ያስመረጡ ምርጫ ወረዳዎች፣ የዕጩዎችን ሰነዶች መላካቸውንና ዕጩዎቹ በጉባኤ የተመረጡ መሆናቸውንና አስመራጭ ኮሚቴዎች ሰነዶቹ ላይ የፈረሙባቸው መሆናቸውን እያረጋገጡ እንደሚገኙ ድርጅት ጉዳይ ኃላፊው ገልጸዋል፡፡

«ምርጫው ላይ ቅሬታ ከቀረበ በምን መልኩ ማጣራት ይቻላል?» ብላ ዜጎች መድረክ ላነሳንላቸው ጥያቄዎች ድርጅት ጉዳይ ኃላፊው፣ በሰጡት ምላሽ በየወረዳው የዲሲፕሊን ኮሚቴ መኖሩንና በምርጫው ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም አካል በወረዳ ደረጃ ለሚገኘው ዲሲፕሊን ኮሚቴ ቅሬታውን ማቅረብ እንደሚችል ገልጸዋል፡፡ በወረዳ ደረጃ ባለው የዲሲፕሊን ኮሚቴ ችግሩ ካልተፈታም ቅሬታውን በማዕከል ሥር ላለው የዲሲፕሊን ኮሚቴ ማቅረብ እንደሚቻል



ኃላፊው ተናግረዋል፡፡

ኢዜማ በምርጫ 2013 ዓ.ም አደረጃጀቱን በዘረጋባቸው 435 ምርጫ ወረዳዎች ዕጩዎችን በማቅረብ ለመወዳደር ዝግጁ መሆኑን የገለጹት ድርጅት ጉዳይ ኃላፊው፣ እስከ 500 ምርጫ ወረዳዎች ላይ ለመወዳደር ዕቅድ እንዳለውም ጠቅሰዋል፡፡

# ኢዜማ በቀጣዩ ሀገር አቀፍ ምርጫ የሴቶች ተሳትፎ እንዲያድግ በከፍተኛ ደረጃ እየሰራ መሆኑን ገለጸ

ጥር 6 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ሴቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ረብዕ ጥር 05 ቀን 2013 ዓ.ም ለሴቶች ስልጠና መስጠቱን የኢዜማ ሴቶች ጉዳይ ተጠሪ ትዕግስት ወርቅነህ ለዜጎች መድረክ ገለጹ፡፡

ቋሚ ኮሚቴው የሰጠው ስልጠና በያዝነው የግንቦት ወር መጨረሻ በሚደረገው 6ኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ ላይ በምርጫ ወረዳ ደረጃ በሚደረገው ፉክክር ሴቶች በዕለቱ በሚደረገው ራስን የማስተዋወቅ የአምስት ደቂቃ ንግግር ላይ ሴቶች ጥሩ ብቃት እንዲያሳዩ የሚያደርግና ጥሩ የንግግር ክህሎት እንዲላበሱ የሚያስችል መሆኑን ተጠሪዋ አስረድተዋል፡፡

ኢዜማ በ2013 ዓ.ም በሚደረገው ሀገር አቀፍ ምርጫ በብቃት አሸናፊ ሆኖ ለመወጣት በየወረዳው ዕጩ ተወዳዳሪዎችን በወረዳ ደረጃ እያስመረጠ የሚገኝ ሲሆን፣




ፓርቲው ከሌሎች ፓርቲዎች በተለየ ለሴቶች እና ለአካል ጉዳተኞች ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ እንደሚገኝ የጠቆሙት ተጠሪዋ፣ ቀደም ብለው የእጩዎች ምርጫ ያደረጉ የኢዜማ ምርጫ ወረዳ ተመራጮች ለሴት ሰልጣኞች ያላቸውን ልምድና ተሞክሯቸውን ማካፈል መጀመራቸውን ገልጸዋል፡፡

ኢዜማ የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳካት ከፍተኛ ሥራ እየሰራ መሆኑን የተሰጠውም ኮታ በትክክል ተግባራዊ ለማድረግ እየሰራ እንደሚገኝ የጠቀሱት የኢዜማ ሴቶች ጉዳይ ተጠሪ ትእግስት ወርቅነህ፣ ፓርቲያቸው ወደ ፖለቲካው ተሳትፎ ለመግባት ለሚፈልጉ ሴቶች በሩን ክፍት አድርጎ እየሰራ እንደሚገኝ፣ ምርጫውን የማይወዳደሩ ሴቶች የፖለቲካ ተሳትፏቸውን ለማስፋት በታዛቢነት ካልሆነም በመራጭነት በንቃት በመሳተፍ በምርጫውም ላይ ከፍተኛ ሚና እንዲኖራቸው ለማድረግ ከፍተኛ ሥራ እየሰሩ እንደሚገኙ አሳውቀዋል፡፡